ደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ
DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA
OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር11 ዎላይታ ሶዶ መጋቢት 23…ቀን ፪ሺ፲፰ዓ.ም ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 11
Wolaita Sodo, 2026

# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት

# አቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር…../2018

**መግቢያ**

የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ብልፅግና በዘላቂነት ለማረጋገጥ የማይተካ ሚና ካላቸው ተግባራት አንዱ ብቃት ያለው አመራር እና ፈጻሚ መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ ተከታታይና ሁሉን አቀፍ የአመራርና ሥራ አመራር ልማት ሥራ በየደረጃዉ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዕዉቀት የተመሰረተ ፍላጎት ተኮር የአመራርና የፈጻሚዎች ስልጠና እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ብሎም ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ሳይንሳዊ የለውጥ ሀሳቦችን በማመንጨት በክልሉ ብሎም በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ የሚያስችል ተቋም አለመኖሩ ኢንስቲትዩቱን በአዲስ መልኩ መቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በክልሉ በተበጣጠሰ መልኩ የሚከናወኑ ስልጠናና አቅም ማጎልበት ስራዎችን በተደራጀ መልኩ የሚሰጥና የክልልሉን ወጪ የሚቀንስ ተቋም በማስፈለጉ፤

በክልሉ የሚተገበሩ የተለያዩ የመንግስት ፖሊሲዎች አተገባበር ክፍቶቶችን በሳይንሳዊ ጥናት እየለየ ለክልሉ መንግስት ምክረ ሃሳብ የሚያቀርብ ተቋም ማስፈለጉ፣

በቀጣይ በክልሉ የሚተገበረው ሪፎርም ተከትሎ የክልሉን መንግስት ሰራተኛ ብቃት የሚመዝንና የብቃት ክፍተት የሚሞላ ተቋም በማስፈለጉ፣

የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2017 አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1፤ አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ **"የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት አቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር"** ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ...../2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2፤ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "**ክልል**" ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ነው፤
2. **"ምክር ቤት"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው፡፡
3. **''ርዕሰ መስተዳድር''** ማለት የክልል ርዕሰ መስተዳድር ነው፤
4. **"መስተዳድር ም/ቤት"** ማለት በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፷፺ የተመለከተው ከፍተኛ የአስፈጻሚ አካል ነው፡፡
5. "**አዋጅ**" ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የአስፈጻሚ ተቋማት መልሶ መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2017 ነዉ፡፡
6. "**ደንብ**" ማለት የክልሉ አቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው ደንብ ነው፤
7. "**ኢንስቲትዩት**" ማለት በዚህ ደንብ የተቋቋመ የክልሉ አቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ነው፤
8. **"ሥራ አመራር ቦርድ"** ማለት ኢንስቲትዩቱን በበላይነት የሚመራና አቅጣጫ የሚሰጥ የስራ አመራር አካል ነዉ፡፡
9. **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት ኢንስቲትዩቱን እንዲመራ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም የተፈጥሮ ሰው ነው፤
10. **''ምክትል ዋና ዳይሬክተር''** ማለት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር የሆነ የተፈጥሮ ሰው ነው፤
11. **"ሥራ አመራር ኮሚቴ"** ማለት በዋና ዳይሬክተር ሰብሳቢነት የኢንስቲትዩቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን በቅርበት እየተከታተለ ውሳኔ የሚሰጥና የሚያስፈፅም ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች እና ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ በአባልነት የሚያካትት አካል ነው፡፡
12. **"አመራር"** ማለት በፖለቲካ፣ በመንግስት፣ በሲቪክ እና በግል ተቋማት ውስጥ በተለያዩ የአመራር ደረጃዎች የሚገኝ የሥራ ኃላፊ ነው፤
13. **"ፈጻሚ"** ማለት በመንግስት፣ በሲቪክ እና በግል ተቋማት ውስጥ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሚያገለግል ሠራተኛ ነው፤
14. "**ማማከር**" ማለት ከችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ውጤት እና ሳይንሳዊ ትንተና ምልከታና ልምድ ላይ ተመስርቶ ለተቋማዊ ለውጥና ውጤታማነት በተለያዩ ዘዴዎች ለተቋማት፣ ለባለድርሻ አካላት፣ ለአመራሩና ፈጻሚዎች የሚሰጥ የሙያ ስልጠናና ምክር አገልግሎት ነው፤
15. "**ሰው**" ማለት ተፈጥአዊ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**አንቀጽ 3፤ የጾታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 4፤ የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት አቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ኢንስቲትዩቱ መቋቋም፣ መቀመጫ፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባርና አደረጃጀት

**አንቀጽ 5; የኢንስቲትዩቱ መቋቋምና ተጠሪነት**

1) የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት አቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት (ከዚህ በኋላ በአጭሩ "ኢንስቲቲዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ኢንስቲቲዩት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

2) ኢንስቲቲዩቱ በሕግና በሙያው የሚኖረው የአስተዳደርና የአካዳሚ ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተጠሪነቱ ለክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 6; የኢንስቲቲዩቱ የሥራ ቦታ/ ዋና መስሪያ ቤት**

የኢንስቲቲዩቱ ዋና መስሪያ ቤት ወላይታ ሶዶ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ አስተዳደር እርከኖች/ክክል ውጪ ቅርጫፎች/ማስተባበሪያዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 7፡ ዓላማ**

ኢንስቲቲዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

1) ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ ያላቸውን የፖሊሲ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ለክልሉን መንግስት አማራጭ የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦችን ማቅረብ፤

2) በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ፣ በንድፈ-ሀሳብ የተደገፈ ተግባር ተኮር፣ ሁሉን አቀፍ እና ተደራሽ የአመራርና የፈጻሚዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ሥርዓት መዘርጋትና ማጠናከር፤

3) ጥናትና ምርምር በማካሄድና የተለያዩ መድረኮችንና ፎረሞችን በማዘጋጀት የክልሉን መንግስት ማማከር፤

4) ዕውቀትንና እውነትን የተላበሱ፣ ለህዝብ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚችሉ፣ በሥራቸውና በምግባራቸው ብቁ አመራሮችንና ፈጻሚዎችን በየደረጃው በብዛት በመገንባት የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ብልጽግና በዘላቂነት ማረጋገጥ፤

5) ወቅታዊ ክልላዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚነሱ ሀሳቦች ላይ ጥናትና ምርምር በማካሄድ፣ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የተለያዩ መድረኮችንና ፎረሞችን በማዘጋጀትና በማማከር የአመራር እና ሥራ አመራር ልማትን ማሳደግ፤

6) የአመራር ልማትና የሥራ አመራር ልማት ሥልጠና፣ ጥናትና ምርምር እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ለተሳካ ክልላዊ ተቋማዊ ግንባታ እውን መሆን ኃላፊነቱን መወጣት የሚችል አመራርና ፈጻሚዎችን በማፍራት ለሀገራዊ የብሔረ-መንግስትና ሀገረ-መንግስት ግንባታ አስተዋጾኦ ማድረግ፤

7) የሀገሪቱን የአመራር ልማት ፖሊሲ ማዕቀፉን መሠረት ያደረገ የአመራር ልማት ሥልጠና በማካሄድ የመንግስት ፖሊሲ ሪፎርም አጀንዳዎች በውጤታማነት መፈጸምና ማስፈጸም የሚችል ብቃት ያለው አመራርና ፈጻሚዎችን ለመገንባት ነው፤

**አንቀጽ 8; የኢንስቲቲዩቱ አደረጃጀትና ተጠሪነት**

1. ኢንስቲቲዩቱ የሚከተሉት የአመራርና የአስተዳደር አካላትን የያዘ አደረጃጀት ይኖሩታል፡፡ እነሱም፡-

   ሀ) የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኃላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

   ለ) በቦርዱ አቅራቢነት የሚሾም የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤

ሐ) የኢንስቲቱዩቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ፤

መ) ብዛታቸው እንደየሰራው አስፈላጊነት የሚወሰን የኢንስቲትዩቱ የሥራ ክፍሎች፤

ሠ) ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች፣ የአስተዳደር እና የቴክኒክ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

2. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ሲሆን የኢንስቲቲዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስቲቲዩቱ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት የሚያከናዉኑ የዓላማ ፈፃሚና የወል ወይም ደጋፊ የስራ ዘርፎች አደረጃጀት አካላትን ያዋቅራል፡፡ ዝርዝሩ ኢንስቲቲዩቱ በሚወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 9; <u>የኢንስቲቲዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኢንስቲቲዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ወቅታዊነቱን የጠበቀና ጥልቀት ያለው ፖሊሲ ጥናትናቶችን ያካሂዳል፤ የፀደቀ የምርምር ውጤት ያሳትማል፤ ያሰራጫል፡፡
2. በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የክልሉን መንግሥት ያማክራል፡፡
3. የየወቅቱ ተጨባጭ ለውጦች የተረዳ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሐሳቦችን ያመነጫል፡፡
4. የመንግሥት ተልዕኮ ለማሳካት የመንግሥት ድጋፍና አመራር ለማጠናከር የሚያግዝ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ተቋማዊ ግንባታ አስመልክቶ መነሻ ሐሳብ ያመነጫል፤ ጥናት ያካሂዳል፡፡
5. በተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አፈጻጸም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን አስመልክቶ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ የመፍትሔ ሐሳብ ያመነጫል፡፡
6. የክልሉን ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ፍላጎት፣ ዕውቀትና ዝግጁነት ያላቸውን ተመራማሪዎችን ያስተባብራል፡፡
7. እንደአስፈላጊነቱ ከዩኒቨርሲቲዎች፤ ከሌሎች የምርምር ተቋማት እና አማካሪዎች ጋር በመተባበር የፖሊሲና ስትራቴጂ ጥናትና ምርምር ያካሄዳል፡፡
8. የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ለማሳደግ የተለያዩ ሴሚናሮችን ወርክ ሾፖችንና የጉባኤ መድረኮችን ያዘጋጃል፤
9. ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶች ካሉአቸው ተቋማትና ታዋቂ ምሁራን ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፡፡
10. ከውጪ ሀገሮች የጥናትና የምርምር ተቋማት ጋር በመሆን ምርጥ ተሞክሮዎችን ይለዋወጣል፣ ይቀምራል፤ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ የጥናትና ምርምር ውጤት ያሰራጫል፡፡
11. ደረጃውን የጠበቀ የአመራር ልማትና ሥራ አመራር ልማት ሥልጠና፣ ጥናትና ምርምር እና የማማከር አገልግሎት ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች፤ ማኑዋሎች፣ ካሪኩለሞች እና ሌሎችንም ስርዓቶችን ይቀርጻል፤ ይተገብራል፤
12. የክልሉን የአመራርና ፈፃሚዎችን የስልጠና ፍላጎትን መሰረት በማድረግ በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ በአመራር ልማት እና በሥራ አመራር ልማት ዙሪያ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ ለሚሰጠዉ ስልጠና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
13. ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ልዩ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ሥልጠናውንም ይሰጣል፤

14. የሰልጣኞች መመልመያ መስፈርት ያዘጋጃል፣ በመስፈርቱ ይቀበላል፣ የዕለት ተዕለት ግንባታቸው ይከታተላል፤ እንደአስፈላጊነቱም ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳል፤
15. ለፈጻሚዎች ብቃታቸውን ለማጎልበትና ለማሳደግ የሚረዱ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ይሰጣል፣ ብቃታቸውን ይመዝናል፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣
16. ለመንግስት መሥሪያ ቤቶች ወይም ተቋማት ወይም ለሲቪክ ማህበራት ወይም ለግል ድርጅቶች በጥናትና ምርምር ምልከታና ትንተና ላይ ተመስርቶ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤
17. በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው የክልሉ እና በሀገር ውስጥ የአቻና ተባባሪ ተቋማት ጋር በመተባበር ሴሚናሮችና፣ ሲምፖዚየሞችን፣ ዎርክሾፖችን፣ ኮንፈረንሶችን ያዘጋጃል፣
18. የአስፈጻሚና የፈጻሚዎችን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የሚያሳድጉ አዳዲስ አሠራሮችን ለመተግበር የሚረዱ የተመረጡ ልምዶችን በመቀመር የዕውቀትንና የልምድ ሽግግር ያካሂዳል፤
19. የኢንስቲቲዩቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል ተቋማዊ የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂ ይቀርፃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ በተፈቀደለት መዋቅር ሥራ መደቦች ላይ ለኢንስቲቲዩቱ የሚያስፈልጉ ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፤
20. የሥልጠና፣ የጥናትና ምርምር እና የማማከር ሥራን በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ይሰጣል፣ ሀገር አቀፍ ተወዳዳሪነቱን ያሳድጋል፤
21. የሠራተኞች መፈጸም አቅም የሚያሳድጉ ለተለያዩ የሙያ ዘርፎች የተለያዩ የባህርያዊ እና ቴክኒካል ብቃት ሞጁሎችን በማዘጋጀት ሞጁላር እና ማሟያ ሥልጠና ይሰጣል፤ የማብቃት አሰራርን ተግባራዊ ያደርጋል፤
22. የክልሉ መንግሥት ሠራተኞች የባህሪያዊ እና የቴክኒካል ብቃት ደረጃቸውን በመመዘን ዝቅተኛውን የማለፊያ ውጤት ላስመዘገቡ ሠራተኞች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤
23. በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ውስጥ ከሚገኙ ተመሳሳይ ተልዕኮና ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር በሥልጠና፣ በጥናትና ምርምር እና በማማከር መስክ የትብብር ግንኙነት ይመሰርታል፤
24. ኢንስቲቲዩቱ ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች እንደአስፈላጊነቱ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣ የውስጥ ገቢ ያመነጫል፣ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ኢንስቲቲዩቱ በሚያወጣው የውስጥ መመሪያ መሠረት አስወስኖ በጥቅም ላይ ያውላል፤
25. በሥራ አመራር ልማት ዘርፍ ለሚሰማሩ የግል አማካሪዎች የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ ሰርተፊኬት ይሰጣል፣ አቅማቸውን ይገነባል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤ በየዓመቱ ያድሳል፤ እንደአስፈላጊነቱ ህጋዊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፡፡
26. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በኢንስቲቲዩቱ ስም ይከሳል፤ ይከሰሳል፣
27. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የኢንስቲትዩቱ የስልጣን አካላት አወቃቀር፣ ሥልጣንና ተግባር</u>

**አንቀጽ 10፤ <u>ስለ ሥራ አመራር ቦርድ መቋቋም</u>**

የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ቦርድ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

1) የኢንስቲትዩቱ ቦርድ ሰብሳቢውን ጨምሮ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ) የክልሉ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ........................................ሰብሳቢ

ለ) የክልሉ መንግስት ዋና ተጠሪ ............................. አባልና ምክትል ሰብሳቢ

ሐ) የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ........................................አባልና ፀሐፊ

መ) የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮምሽነር.................................................አባል

ሠ) የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ.......................................................አባል

ረ) የክልሉ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ...................................አባል

ሰ) የክልሉ ግብርና ቢሮ....................................................አባል ይሆናል፡፡

2) የቦርዱ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 11፤ <u>የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የሥራ አመራር ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

1) የኢንስቲትዩቱን የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ እንዲዘጋጅ በማድረግና ለየኢንስቲትዩቱ ማህበረሰብ በማቅረብና በማጸደቅ ወደ ስራ እንዲገባ ያደርጋል፣
2) የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት፣ አመራርና አሰራር በመፈተሽ ተቋሙ ራዕዩንና ተልዕኮውን በሚመጥን ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል፣ አፈፃጸሙን ይከታተላል፣
3) የኢንስቲትዩቱ የአቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ስራዎች ጥራትና አግባብነት ተከትለው እየተከናወኑ መሆኑን ይፈትሻል፣ አቅጣጫ ማስያዛል፣
4) የአቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ጉዳዮችን በሚመለከትና የኢንስቲትዩቱ ማህበረሰብ የሚተዳደርበትን የውስጥ ደንብ ያወጣል፣ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋልና መከበሩንም ይከታተላል፣
5) በየኢንስቲትዩቱ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባቱንና መልካም አስታዳደር መስፈኑን ያረጋግጣል፣
6) ኢንስቲትዩቱ በሀብት አጠቃቀም ላይ ህጋዊ አሰራሮችን ተከትሎ እንዲሰራና ከኦዲት ግኝት ነፃ እንዲሆን ያደርጋል፣
7) በኢንስቲትዩቱ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንድከስሙ ከየኢንስቲትዩቱ ማህበረሰብና ከሚመለከታቸው ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ይሰራል፣
8) የኢንስቲትዩቱ ራዕዩንና ተልዕኮውን በሚያሳካበት ሁኔታ ስትራቴጅክ ተኮር አመራር ይሰጣል፣
9) በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ የሪፎርም ስራዎችን ልዩ ትኩረት በመስጠት ክትትል ያደርጋል፣
10) ስትራቴጅካዊ ተቋማዊ አቅም ግንባታና ፖሊሲ ጥናት ስራዎች ባግባቡ እንድተገበሩ ያደርጋል፣
11) የኢንስቲትዩቱ የራሱን የውስጥ ገቢ ህጋዊ የአሰራር ስርአት በመከተል እንዲያመነጭ ያደርጋል፣

**አንቀጽ 12፤ <u>የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን</u>**

1) የቦርዱ አባላት የአገልግሎት ዘመን አምስት አመት ይሆናል፤
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የቦርዱ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለተጨማሪ አምስት አመታት ሊራዘም ይችላል፡፡

**አንቀጽ 13፤ <u>የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ ስነ ሥርዓት</u>**

1. ከአባላቱ 50+1 ከተገኘ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
2. የቦርዱ ውሳኔ በአባላቱ አብላጫ ድምፅ ይፀድቃል፤ የአባላቱ ድምፅ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው ሀሳብ አሸናፊ ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 14; የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1) የኢንስቲትዩቱን የረዥምና የአጭር ጊዜ የሥራ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የሥራ መርሐ-ግብርና በጀት ያዘጋጃል፣ ለቦርዱ አቅርቦ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ መርሀ-ግብር መሠረት ሀብትን ያስተዳድራል፤
2) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን የመምራት እና የመወከል ኃላፊነት ይኖረዋል፤
3) የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች፣ መሪ እሴቶችና ድንጋጌዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
4) ኢንስቲትዩቱ ከፌዴራል፣ ከክልል አቻ ተቋማትና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል፤
5) የኢንስቲትዩቱን ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ለቦርዱ በማቅረብ ያስፀድቃል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤
6) የኢንስቲትዩቱ የትኩረት አቅጣጫ፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርዓት አግባብነት ባለው የመንግሥት ፖሊሲ፣ በዚህ ደንብ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባለው ሌላ ህግ መሠረት መቀረፃቸውን ያረጋግጣል፣
7) ለኢንስቲትዩቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣
8) ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ በሆነ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ዳይሬክተሮች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል ወይም ትኩረት ተደርገው የሚከናወኑ ተግባራትን ለይቶ ይሰጣል፤
9) የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይገመግማል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤
10) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለርዕሰ መስተዳድርና ለቦርድ ጽ/ቤት ያቀርባል፤
11) የኢንስቲትዩቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና በቦርድ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

**አንቀጽ 14; የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

1) ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰንና በመንግሥት የሚሾሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚኖሩ ሆኖው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፣
   ሀ) የየዘርፋቸውን ሥራ ያቅዳሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይመራሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣ ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳሉ፣ ያማክራሉ፤
   ለ) በኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት መዋቅር መሠረት የተሾሙበትን የሥራ ዘርፍ በኃላፊነት ይመራሉ፣ ይከታተላሉ፤
   ሐ) በኢንስቲትዩቱ መዋቅር መሰረት በዘርፉ የተደራጁትን ዳይሬክቶሬቶች፣ የሥራ ክፍሎች እና አገልግሎቶችን ሥራ ያስተባብራሉ፤ይመራሉ፤

መ) ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ በሚሰጣቸዉ የውክልና ስልጣን መሰረት ዋና ዳይሬክተሩን ተክተው ይሰራሉ፣

ሠ) የየዘርፋቸውን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅተው ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባሉ፣

ረ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናሉ፡፡

1) የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 15; የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ፡-**

የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ በዋና ዳይሬክተር ሰብሳቢነት የኢንስቲትዩቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን በቅርበት እየተከታተለ ውሳኔ የሚሰጥና የሚያስፈፅም ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች እና ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ በአባልነት የሚያካትት አካል ነው፡፡

**አንቀጽ 16; የኢንስቲትዩቱ የሥራ ክፍሎች**

የኢንስቲትዩቱ አላማ ፈጻሚና እና ሌሎች የወል ሥራ ክፍሎች የሚኖሩት ሲሆን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር እና አሰራር በሚመለከት ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣዉ የኢንስቲትዩቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 17; በጀት**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት የበጀት ምንጮች ይኖሩታል፡፡

1. ከክልሉ መንግሥት የሚመደብ በጀት፣
2. ኢንስቲትዩቱ ከሚያስከፍለው የአገልግሎት ክፍያዎች፣
3. ከሌሎች ምንጮች በሚገኝ ገቢ፣

**አንቀጽ 18; የበጀትዓመት**

የኢንስቲትዩቱ የበጀት ዓመት በየዓመቱ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ድረስ ያበቃል፡፡

**አንቀጽ 19; የሂሳብ መዛግብትንና የሂሳብ ምርመራ**

1) ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2) የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራል፡፡

**አንቀጽ 20; የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 21; ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ሲሰራባቸው የቆዩና ከዚህ ደንብ ጋር የማይጣጣሙ ወይም የሚቃረኑ ማንኛውም ሕግ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**አንቀጽ 22; ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1) መስተዳደር ምክር ቤቱ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣
2) ቦርዱ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
3) ኢንስቲትዩቱ ደንቡንና ደንቡን ተከትሎ የሚወጣውን መመሪያ ለማስፈጸም የሚረዳውን ዝርዝር የውስጥ አሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 23; አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከጸደቀበት ከዛሬ መጋቢት/...... 2018 ዓም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ወላይታ ሶዶ**

**መጋቢት..../2018 ዓም**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር**